በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 211689
ግንቦት 29 ቀን 2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የደቡብ ክልል ዐ/ሕግ

ተጠሪዎች፡-1) በረከት በየነ

2) ተስፋዬ ጋልቾ

} የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34474 ግንቦት 6ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ የሰው መግደል ወንጀል የሚመለከት ክስን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነበር፡፡ የአሁን አመልካች ጳጉሜ 4ቀን 2011ዓ/ም በተፃፈ ክሱ 1ኛ ተጠሪን 3ኛ ተከሣሽ 2ኛ ተጠሪን ደግሞ 5ኛ ተከሣሽ በማድረግ ተጠሪዎች ከሌሎች ተከሣሾች ጋር ሆነው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 540 የሚደነግገውን ተላልፈው የካቲት 24ቀን 2011ዓ/ም ከምሽቱ በ2ሰዓት አረካ ከተማ ቀበሌ 04 ትምህርት ቤቶች ፅ/ቤት ፊት ለፊት ሚች አዲሱ በለጠን 4ኛ ተከሣሽ ስሙን ጠርቶ እንዲቆም አድርጎ

ለስላምታ የሚችን እጅ ጨብጦ እንደያዘው፤ 1ኛ ከሣሽ ከኋላ በኩል በፌሮ ብረት የኋላ ጭንቅላቱን 2 ጊዜ ሲመታው፤ 2ኛ ተከሣሽ በጌጠኛ ድንጋይ (ኮብል ስቶን) የግራ ጭንቅላቱን 3ኛ ተከሣሽ(1ኛ ተጠሪ ) የሚችን ጀርባ በክራንች ሁለት ጊዜ፤ 5ኛ ተከሣሽ(ሁለተኛ ተጠሪ) ሚቹ እንደወደቀ ጉረሮውን እና ሆዱን ከረገጠው በኋላ ሮጠው ማምለጣቸውን ሚች በድብደባው ስለደከመ በዱቦ ሆስፒታል ሲታከም ቆይቶ መጋቢት 5ቀን 2011ዓ/ም መሞቱን በመዘርዘር የሰው መግደል ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ክስ አቅርቦባቸዋል፡፡ ተጠሪዎችና ሁሉም ተከሣሾች ክደው በመከራካራቸው አመልካች ክሱን ለማስረዳት ምስክሮቹንና የሕክምና ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪም በበኩላቸው መከላከያ ምስክሮችን አቅርበዋል፡፡

ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የግራቀኙን ማስረጃ መርምሮ የዐ/ህግ ምስክሮች በወንጀሉ ቦታ ነበር ብለው ተከሣሾች

እያንዳንዳቸው የፈፀሙትን ድርጊት የገለፁ ቢሆንም የሰጡት ምስክርነነት ቃል ልዩነት ያለበት ተመሣሣይ አለመሆኑን ለአብነት ያህልም፡- አንደኛ ምስክር የካቲት 23 ሄደው አድረው የካቲት 24 እንደተመለሱ ሲመሰክር ሁለተኛ ምስክር ደግሞ የካቲት 24 ሄደው በእለቱ መመለሣቸውን፤ 1ኛ ምስክሯ ለቤቱ ምርቃት የደስ ደስ ቅቤ ይዛ መሄዷን ሚች አንድ ሽህ ብር እንደሰጠ ሌሎች ግን አለመስጠታቸውን ስትመሰክር ሁለተኛ ምስክሩ ደግሞ ሁሉም ገንዘብ ብቻ እንደሰጡ መስከራቸው ለልዩነቱ ማሣያነት ተጠቅሰዋል፡፡ በሌላ በኩል ጩኸት ተሰምቶ የመጡትን የአካባቢው ሰዎች በጨለማ ምክንያት ለመለየት አለመቻላቸውን ከገለፁ በኋላ የተጠሪዎችን ግን መለየታቸውን መመስከራቸው እንዲሁም የፈፃሚዎችን ማንነት ለይተው በእለቱ ለፖሊስ ማስመዝገባቸውን የመሰከሩ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ባደረገው ማጣራት ለፖሊስ አለማስመዝገባቸው ማረጋገጡ ተዓማኒነታቸውን የሚያጠራጥር መሆኑን ጠቅሶ በጥቅሉ የአመልካች ምስክሮችም የሚች ወንድም እና እህት መሆናቸውም ተጠቃሎ ሲታይ በመመካከር የመሰከሩ መሆናቸውን ማመኑን ተጠሪዎች በበኩላቸው ባቀረቧቸው መከላከያ ምስክሮች የአመልካችን ምስክሮች ማስተባበላቸውን ጠቅሶ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 149(2) መሰረት በነፃ እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡

ይህን ውሣኔ መሰረት በማድረግ በአመልካች ይግባኝ ባይነት ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት 1ኛና 2ኛ ተከሣሾች የነበሩት መልስ ሰጪዎች በሌሉበት የአሁን አመልካችንና ተጠሪዎችን የይግባኝ ክርክር እንዲሁም ማጣሪያ ምስክር አዳምጦ ከመረመረ በኋላ አንደኛ ተጠሪ በእግሩ ላይ ቀዶ ጥገና ተደርጎለት እናቱ ቤት የነበረ ስለመሆኑ በመከላከያ ማስረጃ አረጋግጣለሁ ብሎ ጭብጥ አስይዞ መከላኪያ ምስክሮች የሰጡት ቃል እና የሕክምና ማስረጃው በሌላ ቀን እንደተመረመረ የሚገልፅ መሆኑን የሚያሳይ ነው ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ ይግባኝ ያልተጠቀበት 4ኛ ተከሣሽ ሲቀር ሌሎችን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ)ና 540 ጥፋተኛ ብሎ የአሁን አንደኛ ተጠሪ በአስር ዓመት ፅኑ እስራት ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ተሣትፎውን መሰረት በማድረግ በአምስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

ይህ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ያሉት ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ችሎቱ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮ በተጠሪዎች ላይ የጥፋተኝነት የመወሰኑን አግባብት ከማስረጃ ምዘና አንፃር ከመረመረ በኋላ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የተደመጡት ሁለት ማጣሪያ ምስክሮች የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሊያስለውጥ የሚችል ምስክርነት አለመስጠታቸውን፣ ችሎቱም ያረጋገጡለትን ፍሬ ነገር በፍርዱ ላይ አለማስፈሩን፣ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የዐ/ሕግ ምስክሮች የሰጡት ቃል ከመመዘን ይልቅ ተጠሪዎች መከላከያ ምስክሮች ላይ ማተኮሩን፤በስር ፍርድ ቤት 4ኛ ተከሣሽ የነበረው መጀመሪያ ለሟች በተደጋጋሚ ስልክ ደወለ በኋለም እጁን ይዞ ማስመታቱ በዐ/ህግ ምስክሮች ተረጋገጠበት የተባለው ተከሣሽ ወንጀሉ ሲፈፀም ቦታው እንዳልነበረ ተከላክሏል በሚል በስር ፍርድ ቤት የተወሰነውን ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አጽንቶ ሌሎችን ጥፋተኛ ናቸው ያለበትን ምክንያት በግልፅ አለመመዝገቡን፣ እንዲሁም ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት ሰዓት ከሟች ጋር ነበሩ የተባለው አምስት ወንድም እና እህቶች ሟች ሲደበደብ በፍርሀት ምክንያት እየሮጡ ወደ ቤታቸው መግባታቸውን የገለፁትን ምስክርነት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ማመኑ፤ተጠሪዎች በኩል ሟች ጠጥቶ ዲች ውስጥ ውድቆ እንደሞተ በከተማው መወራቱን በመከላከያነት ያላቀረቡት ቢሆንም ሟችና ተጠሪዎች ለድብድብ የሚያበቃ ፀብ ያልነበራቸው መሆኑ ተደምሮ ሲታይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማስረጃውን በአግባቡ ሣይመዝን ጥፋተኛ ማለቱ ገቢነት የለውም ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ስላፀናው አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ሐምሌ 21ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው በማስረጃ ምዘና መርህ የዐ/ህግ ማስረጃ ሊመዘን የሚገባው ሙሉ ይዘቱ እንጅ ለክሱ መሰረታዊ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ የተፈጠረ ልዩነቶች ላይ ብቻ አተኩሮ ማስረጃን በመመዘን ተከሣሾች በነፃ እንዲሰናበቱ መወሰኑ የማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርሆዎ ችን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መሆኑን ዘርዝሮ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከቀረበባቸው ክስ ተከላክለዋል ሲል በነፃ ያሰናበተበትን አግባብነት ከወ/ሕ/ቁጥር 23(2)ና 540 ድንጋጌ አኳያ እንዲመረመር ጉዳዩ ቀርቦልናል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይሁን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፈፀሙት መሰረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘና የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ፣ የአመልካችን የሰበር ቅሬታ እና በማስቀረቢያ ነጥቡ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ነበር፡፡ በመሆኑም አመልካች ከሚያቀርበው ክርክር በመነሣት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከቀረበባቸው ክስ በነፃ እንዲሰናበቱ በሰጡት ውሣኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ለመወሰን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ተምርምሯል፡፡

እንደተመረመረው ተጠሪዎች ከሌሎች ተከሣሾች ጋር በመሆን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅመዋል ሲል ክስ አቅርቦባቸው ክደው ተከራክረዋል፡፡ በአመልካች ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሟች ቤተሰብ የሆኑ ሁለት ምስክሮችን እና የሕክምና ማስረጃ አቅርቧል፡፡ በቀረበው የወንጀል ክስ ላይ የተካደ ፍሬ ነገርን በማስረጃ አጣርቶ ማስረጃውንም መዝኖ እንዲወስን የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሲመዝን ምስክሮች በእለቱ ለፖሊስ

አስመዝግበናል ሲሉ  የሰጡት ምስክርነት ሐሰነት መሆኑ በፖሊስ መረጋገጡን፣ ምስክሮች በሰጡት ምስክርነት የፈጠሩት ልዩነትን፣ ምስክሮች ከሟች ጋር ካላቸው ቅርብ የስጋ ዝምድ በአንድ በኩል በሌላ በኩል የተጠሪዎች መከላከያ ምስክሮች ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ ተጠሪዎች በቦታው አለመኖራቸውን እምነት ሊጣልበት በሚችል አኳኊን ማስረዳታቸውን መሰረት በማድረግ ተከላክለዋል ሲል በነፃ አሰናብቷል፡፡

ይህን ውሣኔ በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በራሱ ያዳመጣቸውን ማጣሪያ ምስክሮች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር በዝርዝር ሣይገልፅ የተጠሪዎች መከላከያ ምስክሮች በሰጡት ምስክርነት ተፈጥሯል የተባለውን ልዩነት መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች አልተከላከሉም ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ ሰበር  ሰሚ ችሎቱ በበኩሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመሻር በስር ፍርድ ቤት የተሰሙት ምስክሮች የሰጡትን ምስክርት መዝኖ የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት የለውም፤ ይልቁንም ሰበር ሰሚ ችሎቱ የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ምስክሮች የሰጡት ምስርነት ቃል በመመካከር ላይ የተመሰረተ ነው ሲል ከያዛቸው ምክንያቶች በተጨማሪ የራሱን ምክንያት በመጨመር የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሣኔ አፅንቷል፡፡

በየደረጃው የሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረውን ክርክር መርምረው የሰጡት ውሣኔ ቢለያዩም ለውሣኔቸው መሰረት የሆነው ግን በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ማስረጃ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች የተለያዩት በማስረጃ ምዘና እንጅ በሌላ የሕግ አተረጓጎም ወይም በክርክር አመራር ወይም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሊባሉ በሚችሉ ጉዳዮች አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን የመጨረሻ ውሣኔ በተሰጣቸው ማናቸውም ጉዳዩች ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተትን ማረም እንደሆነ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3) ይደነግጋል፡፡ አንድ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚያሰኘው በአዋጅ ቁጥር 1234/2014 አንቀጽ 2(4) የተዘረዘሩት መመዘናዎችን የሚያሟላ ስህተት ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

በዚህ የሕግ መመዘኛ መሰረት የአመልካች ክርክር በየደረጃው የሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ላይ የደረሱበትን መደምደሚያ መለያዬት መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1234/2014 አንቀጽ 10(ሐ) እንደተደነገገው የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚጥስ ውሣኔ መሆኑን ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል የሰጠውን አስገዳጅ ውሣኔ የሚጥስ ውሣኔ መሆኑን አለያም በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 2(4)(ለ) እንደሚደነግገው ሕግን አላግባብ በመተርጎም ወይም ለጉዳዩ ተገቢነት የሌለውን ሕግ በመጥቀስ የተሰጠ ውሣኔ ስለመሆኑ የሚያሣይ ክርክር አላቀረበም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ተወስኗል፡፡

## <u>ውሣኔ</u>

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እ ንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1) የደ/ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34474 ግንቦት 6ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ በወ/መሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(ለ)(2)(ለ መሰረት ፀንቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

ማ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም